# እጅግ አስደንጋጩ የወያኔና የመናፍቃን የጋራ ዘመቻ ድል!

ለኑሮው፣ ለግል ጥቅሙ፣ ለሆዱ ያደረው እግዚአብሔርን ጨርሶ የረሳው የዚህ ዘመን ስመ ክርስቲያን እውነቱ ይሄ መሆኑን በሚገባ ቢያውቅም ማመን ግን አይፈልግም፡፡ እንዳልሰማ እንዳላየ እንደማያውቅ አንድ ነገር በታየ በተሰማ ቁጥር አንዳች ነገር ማድረግ ይችል ይመስል ይንጫጫል፡፡ መንጫጫቱም ከአንድ ሰሞን ወሬነት የሚያልፍ አይደለም፡፡ መፍትሔ ለመተለም አይሞክርም ጨርሶም አያስብም፡፡

ሰሞኑን ያ ገልቱ አባዱላ ገመዳ የተባለ ነፈዝ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባለው የአፈ ጉባኤነት የሥልጣን ወንበሩ ላይ እንደሆነ ሆኖ ሕገ ወጥ የሆነ ተግባር በምዕራባዊያን የመናፍቃኑ ሐሳዊያን መምህራንና የግብረ ሰዶም ሰባክያን ሥርዓተ አምልኳቸውን ሲፈጽሙ የሚያሳይ ፎቶ (ምስለ አካል) በመናፍቃኑ ድረ ገጽ ላይ መለቀቁን ተከትሎ ሰዉ መጽሐፈ ገጽን (ፎስ ቡክን) ጨምሮ በማኅበራዊው የብዙኃን መገናኛ እየተቀባበለ “በመንግሥት ተቋም ላይ እንዴት እንዲህ ያለ ተግባር ይፈጸማል! እነዚህ ሰዎች ባለሥልጣናቱን በሙሉ ተቆጣጥረዋቸዋል ማለት ነው? ሰውየው እንዴት እንዲህ ያለውን ከሕገ መንግሥታቸው ጋር በግላጭ የሚጋጭ ተግባር በድፍረት ሊፈጽም ቻለ?” ምንትስ እየተባለ ሲተች መሰንበቱን ሁላችንንም እናውቃለን፡፡

ወያኔ በመርሐ ባለሥልጣናቱም ሆኑ አባሎቹ ሃይማኖተኛ እንዲሆኑ አይፈቅድም ነበር፡፡ አንዴ ምን ገጠመኝ መሰላቹህ ታስታውሱ እንደሆነ በ 1993 ዓ.ም. ላይ እዚህ አዲስ አበባ ማኅደረ ስብሐት ቅድስት ልደታ ለማርያም ቤተክርስቲያን አሥተዳደር ካህናትና ምእመናን አባ ጳውሎስ በቅድስት ቤተክርስቲያን ላይ እየፈጸሙት የነበረውን የአሥተዳደር በደል ሙስናና ኑፋቄ በመቃወምና በነዚህም ችግሮቻቸው ምክንያት መንፈሳዊና ሞራላዊ (ቅስማዊ) ብቃት ስለሌላቸው ቅድስት ቤተክርስቲያንን ሊመሩ ፈጽሞ የማይገባቸው ሰው በመሆናቸው ሊመሩ አይገባም በማለት ቤተክርስቲያንን ከፋፍሎ ለሌላ ችግር እንደሚዳርግ እያወቅን ነገር ግን ሌሎች አብያተክርስቲያናትን ለማነሣሣትና የሰውየውን የግፍና የክህደት አሥተዳደር እንዲያከትምለት ለማድረግ በማሰብ እርምጃችን ትክክል እንዳልሆነ እያወቅን የልደታ ቤተክርስቲያንን ከእሳቸው አሥተዳደር ገነጠልን፡፡

ጉዳዩ ሃይማኖታዊ እንደመሆኑ ወያኔን የሚያገባው ጉዳይ ባይኖርም እሳቸው ተነኩ ማለት እሱ ተነካ ማለት በመሆኑ ወዲያውኑ ጣልቃ ገባ፡፡ እኛም ሁከት ይታገድልን ብለን ፍርድቤት ክስ መሠረትን፡፡ አሁንም ፋይዳ እንደሌለው እያወቅን አስተዳደራዊ በሆነው ጥፋቶቻቸውና በሙስናቸው ላይ ሰውየውን ከፍተኛ ፍርድቤት ክስ መሠረትንባቸው፡፡

በመሀል የፌደራል ጉዳዮች ሚንስቴር ጉዳዩን ያዘውና ሊያደራድረን ሞከረ፡፡ በዚያን ወቅት ሚንስትሩ አቶ ዓባይ ፀሐዬ ሲሆኑ ምክትላቸው ደግሞ የገቢዎችና ጉምሩክ ሚንስትር የነበሩት አቶ መላኩ ፈንታ ነበሩ፡፡ አደራዳሪያችን እሳቸው ነበሩ፡፡ እኛን አዋክቦ እጅ እንድንሰጥ ለማድረግ ነው እንጅ የድርድር ቅርጽ አልነበረውም፡፡ ከልደታ ቤተክርስቲያን ተወክለን እኔ ከሌሎች ሦስት አባቶች ጋር ሆነን የሚንስቴር መሥሪያቤቱ ድረስ ሔድን፡፡

አቶ መላኩ ፈንታ በትክክለኛ የአደራዳሪነት አቀራረብ ቀርበው አነጋገሩን፡፡ ሌላኛው ቀን ላይ ያሉንን መረጃዎች ሁሉ ይዠ እሳቸው እንደ ክርስቲያንነታቸው ቤተክርስቲያንን የመርዳት ግዴታ እንዳለባቸው አስታውሸ ጉዳያችን በአግባቡ እንዲስተናገድልን እንዲያደርጉ ወተወትኳቸው፡፡ የመረጃዎቻችንን ተጨባጭነትና እውነት ያለን መሆኑን በሚገባ የተረዱት ምክትል ሚንስትሩ ጨነቃቸውና ምን አሉኝ “አምሳሉ ሁሉንም ነገር ተረድቸሃለሁ ግን እኔ ሃይማኖተኛ እንድሆን ድርጅቴ አይፈቅድልኝምና አድርግ የምትለኝን ለማድረግ አልችልም!” አሉኝ፡፡

ምን ለማለት እንደፈለጉ ገባኝ፡፡ ምክንያቱም እኔ አግባብ ያልሆነ ጥያቄ አልጠየኳቸውም፡፡ ጉዳያችን በአግባቡ እንዲያዩልን እንዲተባበሩን ነው የጠየኳቸው፡፡ ክርስቲያን ባይሆኑም ይሄንን ማድረግ ግዴታቸው ነበር፡፡ ይሁንና እሳቸው ማለት የፈለጉት “በክርስቲያንነቴም ጉዳዩን በአግባቡ የማየትና የማስተናገድ ግዴታ ቢኖርብኝም ድርጅቴ ስለማይፈቅድልኝ ይሄንን ነገር ከኔ አትጠብቅ!” ነው ማለት የፈለጉት፡፡ ፍትሕ የለምና “ፍርድቤት ውሳኔ ሰጥቷል!” ብለው መጨረሻ ላይ እንደምታስታውሱት 1995 ዓ.ም. ከላይ እስከታች በመከላከያ አልባሳት የተሸፋፈኑ በሸዎች የሚቆጠር አረመኔ የፌዴራል ፖሊሶችን በእኛ ላይ በማፍሰስ የሃይማኖት አባት አላሉ ሕፃናት እንደጉድ ቀጠቀጡን አሰሩን ሌላም ሌላም የግፍ እርምጃ ነበር የተፈጸመብን፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አባል እንደሆኑ የሚታወቁ ወይም የሚገመቱ የወያኔ ባለሥልጣናት በባለሥልጣንነታቸው ቤተክርስቲያን ለሚደርስባት ችግር ሁሉ በአግባቡ እንድትስተናገድ አያደርጉም፡፡ ምክንያቱም ድርጅታቸው በቤተክርስቲያን ላይ የራሱ የሆነ የጥፋት ዓላማ አለውና፡፡ መናፍቃንና እስላም መሆናቸው የሚታወቁ የወያኔ ባለሥልጣናት ግን ሥልጣናቸውን በመጠቀም አግባብ ያልሆነ ብቻ ሳይሆን ሙሉ ለሙሉ ሕገ ወጥ የሆነ ጥቅም ለእየእምነቶቻቸው ያበረክታሉ፡፡ አቶ አባዱላ ሲያደርጉት ያየነው ይሄንን ነው፡፡ ድርጅታቸው ይሄንን እንዲያደርጉ ይፈቅድላቸዋል፡፡ የጥፋት ዓላማውን ለማሳካት፡፡ እያንዳንዳችን ይህ ኢፍትሐዊ የአስተዳደር በደል በቤተክርስቲያን ላይ ሲደርስ እንደቆየ በሚገባ እናውቃለን፡፡

ስለሆነም አባዱላ እንዲህ አደረጉ እያለ የተቸውን ሁሉ “አስመሳይ ሌባ!” ልለው እወዳለሁ፡፡ መናፍቃኑ አይደለምና “…የኦርቶዶክስን አከርካሪ ሰብረናን” እያሉ በአደባባይ ነውረኛ ጀብዳቸውን እየተናገሩ ያሉትን የአገዛዙን ባለሥልጣናት ይቅርና ቤተክርስቲያንን ከከፍተኛ የሥልጣን ቦታዋ ጀምሮ እስከ ታችኛው ድረስ ተቆጣጥረው በግላጭ በአደባባይ የጥፋት ሥራቸውን መሥራት ከጀመሩ ስንት ዘመን እንዳላቸው እያንዳንድህ በሚገባ ታውቅ አይደለም እንዴ? የምን ማስመሰል ነው! ለኑሮህ፣ ለሆድህ፣ ለግል ጥቅምህ አድልተህ የነፍስህንና የተጣለብህን ክርስቲያናዊ ግዴታ ወርውረህ ጥለህ፣ የሥጋዊ ጥቅምህ በልጦብህ ሰምተህ እንዳልሰማህ ዓይተህ እንዳላየህ ሆነህ እያሳለፍክ እንጅ ይሄንን አታውቅምና ነው?

ሙቱ የወያኔ ተኩላ አባ ጳውሎስ በሞቱበት ዓመት ለመጨረሻ ጊዜ በተሳተፉበት “የሲኖዶስ” ስብሰባ ከመናፍቃኑ ጋር እየዶለቱ ተባብረው የሚሠሩት የቤተክርስቲያንን የደም ስር የሚቆርጥ፣ መንጋዋን በተኩላት የሚያስበላ፣ ቅጥሯን የሚያፈርስ፣ አስተምህሮዋን የሚበርዝ የሚለውጥ የተኩላ ሥራቸው በመታወቁ አንዳንድ የሲኖዶስ አባላት ከመጠየቅ ውጪ ሊያደርጉ የሚገባቸውን እርምጃ ባይወስዱም “ለመሆኑ ሃይማኖትዎ ምንድን ነው?” ብለው መጠየቃቸውን አታውቅምና ነው? ከዚህ ነውረኛ ተግባራቸው በላይ “አይ እኔ መናፍቅ ነኝ የምሠራውም ለመናፍቃኑ ነው” እንዲሉ ነበር የምትጠብቀው?

ተተኪው ተኩላ አባ ማትያስ ይሄንን ተልእኮ አጠንክረው በመቀጠል በግላጭ እዛው ቤተክህነት ሰርገው ከገቡ መናፍቃን ጋር እየሸረቡ የሚሠሩትን ሥራ አታውቅምና ነው? እሳቸውማ እንዲያውም “ከካቶሊኮች ጋር አንድ ነን!” ብለው በአደባባይ እስከመናገር ደርሰዋል፡፡ አንተን ግን ምንም የተሰማህ ነገር የለም፡፡ ቆይ ከዚህ በላይ ምን እንዲሉ ነው የምትጠብቀው? “አንድ ነን!” ማለት ምን ማለት ነው?

ማኅበረ ቅዱሳንን የሚያሳድዱትና ሳያፈርሱት ሳያጠፉት መተኛት እንደማይፈልጉ በአደባባይ የሚዝቱት በምን ምክንያት ነው? በቀኖናዊ ወይም ዶግማዊ ምክንያት ነው? ሰውየው “በዚህ በዚህ ቀኖናዊ ወይም ዶግማዊ ጥፋታቸው ምክንያት ነው ማኅበረ ቅዱሳን ለቤተክርስቲያን አደጋና ጠላት ስለሆነ የማፈርሰው፣ ላጠፋው የምፈልገው፣ ሥራውንም እንዳይሠራ እያደረኩት ያለሁት” ሲሉ ዓይተህና ሰምተህ ታውቃለህ?

የግጭቱ ወይም ያለመግበባባቱ ምክንያት ይሄ ካልሆነስ ሌላ ምንድን ነው? እነ አባ ማትያስን ማን አዟቸው፣ ማን ቀጥሯቸው፣ ለምን ዓላማ፣ የማንን ጥቅም ሊያስጠብቁ ነው ከሕገ ቤተክርስቲያን ውጪ ይሄንን እያደረጉ ያሉት? ቤተክርስቲያን የመናፍቃን የከሀድያንና የአላውያን መፈንጫ መቀለጃ መጫዎቻ ስትሆን በዝምታ ከመመልከት ወይም አብረህ ከማጫፈር በዘለለ “ክርስቲያን ነኝና የቤተክርስቲያኗ ጉዳይ ያገባኛልና ቤተክርስቲያንን ከመናፍቃን፣ ከከሀድያን፣ ከአላውያን የመጠበቅ ክርስቲያናዊ ግዴታ አለብኝና ይመለከተኛል!” ብልህ ሔደህ “ለምንድን ነው እንዲህ የሚደረገው? ሕገ ቤተክርስቲያን ይከለክላልና የቤተክርስቲያንን ጥቅም ይጎዳልና እንዲህማ ልታደርጉ አትችሉም!” ብለህ ጠይቀህ “እኛ መንጋውን ጠባቂ እረኛ መስለውን ነው እንጅ የበግ ለምድ ለብሰው የገቡ ተኩላና ቤተክርስቲያንን አጥፊ የመናፍቃን ቅጥረኛ መልእክተኛ ከሆኑማ ቦታዎ እዚህ አይደለምና ቤተክርስቲያናችንን ለቀው ይውጡልን! ይወገዱልን!” ብለህ ታውቃለህ ወይ? እነሱማ ምን ያርጉ ታዲያ! ያለ ከልካይ ሃይ ባይና ተቆርቋሪ እንደፈለጉ የሚፈለጩበት በረት ሲያገኙ፡፡

አሁንማ ጦርነቱ አልቋል፡፡ እጅ እና እግሩን ተቀፍድዶ የተያዘ ሰው ከመታረድ በስተቀር ምን አማራጭ አለው? የተዋጋቸውም የለ ገብተው ተቆጣጥረውታል፡፡ ከዚህ በኋላማ ምርት የሚያፍሱበት አንተም በመተኛትህ ምክንያት እጅና እግርህን ተቀፍድደህ እንደመያዝህ የምትታረድበት ዘመን ነው፡፡

ከዓመታት በፊት መጽሔቶች ላይ በጻፍኳቸው ጽሑፎች ላይ ከገጠር እስከከተማ ምእመናን በተኩላት ተነጥቀው ማለቃቸውን ጨርሶ ከማለቁና ቤተክርስቲያን ከመጥፋቷ በፊት ማድረግ ያለብንን እንድናደርግ በተከታታይ እሪ ብየ ጮኼ ነበር፡፡ እያንዳንድሽ ለሆድሽ ለጥቅምሽ ስትይ ጆሮ ዳባ ልበስ ብለሽ ነው የተኛሽው፡፡ አልሰማም አላይም ብለሽ ተኝተሽ ለተበላሽው ማንን ተጠያቂ ልታደርጊ ነው አሁን ለማስመሰል የምትንጫጭው**?**

ምን ብየ እንደነበር ላስታውሳቹህ?፦

በደርግ ዘመን በተደረገው የኢትዮጵያ ሕዝብና ቤት ቆጠራ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን አባላት ቁጥር ከአጠቃላዩ የኢትዮጵያ ሕዝብ 54% ያህሉ ነበር፡፡ መናፍቃኑ ደግሞ ባጠቃላይ ማለትም ፕሮቴስታንቶቹና ካቶሊካዊያኑ (በእርግጥ ካቶሊካዊያኑ ድሮም አሁንም ቁጥራቸው አናሳ ነው ከአምስት መቶ ሽህ አላለፉም ይሁንና እነሱንም ጨምሮ) 6.4% ነበሩ፡፡

በዘመነ ወያኔ በ 1987 ዓ.ም በተደረገው የሕዝብና ቤት ቆጠራ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር 53 ሚሊዮን (አእላፋት) ነው ሲል ከ 53 ሚሊዮኑ (አእላፋቱ) የኢትዮጵያ ሕዝብ 27 ሚሊዮኑ ወይም 50.6% የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ተከታይ ነበር፡፡ የመናፍቃኑ ደግሞ እድገት አሳይቶ 10.5%

ወያኔና መናፍቃኑ እስከ 1999 ዓ.ም. ቆጠራ ድረስ በሠሩት ጠንካራ ሥራ በ 1999 ዓ.ም. በተደረገው ቆጠራ ደግሞ አስቀድሞ ከነበረው የእድገት ምጣኔ አንጻር ከ 73 አእላፋቱ (ሚሊየኑ) የኢትዮጵያ ሕዝብ 38 ሚሊዮኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ተከታይ መሆን ሲኖርበት 32 ሚሊየኑ (አእላፍቱ) ማለትም በ 1987 ዓ.ም ቆጠራ ከነበረበት ከ 50.6% ወደ 43% ወርዶ 7.6% በደርግ ጊዜ ከነበረው ደግሞ 11% ምእመናን እንዲበሉባት ሲደረግ መናፍቃኑ ደግሞ በደርግ ዘመን ከነበሩበት ከ 6.4% ወደ 19.2% ማሻቀብ ችለዋል፡፡ ይህ ቁጥር ከየትም የመጣ ሳይሆን በግልጽ ማየት እንደሚቻለው ከኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የተበሉ የተወሰዱ ምእመናን ናቸው፡፡ ልብ በሉ ይህ የሆነው እስከ 1999 ዓ.ም ባለው ቆጠራ ብቻ ነው፡፡

መርዶው ግን ይሄ አይደለም፡፡ መርዶው በየቆጠራው የነበሩበትን እጥፍ እያደኑ እንደመምጣታቸው ቆጠራው በሚሰጠን ሬሾ (የእድገት ምጣኔ) ሒደን ስናሰላው አሁን ላይ ያላቸው ቁጥር (ቆጠራ የሚደረግበትን ዓመት በየምክንያቱ መደረግ ከነበረተት እንዲዘገይ እያደረጉት ነው፡፡ አሁን ደግሞ ከሁለት ዓመት በኋላ ይደረጋል ብለዋል) እንደተባለው በዚያ ዓመት በሚደረገው ብሔራዊ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ያለውን የእድገት ምጣኔ (ሬሾ) ተከትለን ስንገምት መናፍቃኑ 38.4% እስከ 40% የሚሆነውን (ምክንያቱም ከብዙ መብዛት ከጥቂት እንደመብዛት ከባድና አስቸጋሪ ስለማይሆን ይህ ሁኔታ የእድገት ምጣኔያቸውን ከነበረው ቀይሮት እንዲህ ዓይነት ውጤት ሊያመጣ ይችላልና ነው) የኢትዮጵያን ሕዝብ እንደሚይዙ ሲገመት የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ምእመናን ደግሞ ከ 22-20% አሽቆልቁሎ ሊገኝ የሚችል ምናልባትም ከዚህም ወርዶ ሊገኝ የሚችል መሆኑ ነው እጅግ አሳዛኙ መርዶ፡፡

መርዶው ገና አላለቀም እንዳልኳቹህ የመናፍቃኑ የእድገት ምጣኔ (ሬሾ) እንደ ቫይረስ (ጠንቀኛ ተሕዋስ) ራሱን በእጥፍ እያሳደገ እንደመምጣቱ ቀጣይ የኢትዮጵያ ሕዝብና ቤት ቆጠራ ከመደረጉ አምስት ዓመታት በፊት ማለትም 2014 ዓ.ም. አካባቢ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ተከታዮች ባዶ ወይም ምንም ይሆናሉ ወይም የሰይጣን ጀሮው ይደፈንና ቤተክርስቲያን ትጠፋና ኢጋንንት ቦታውን ይይዛሉ፡፡ ነበር ያልኩት

ያኔ እኔ ይፋዊ መረጃ ጠቅሽ ስናገር ሳታምን መናፍቃኑ PentecoStudies በተሰኘ መጽሔታቸው “While estimated to account for less than 1 per cent of the population in the early 1960s,1 Protestants were recorded at 5.5 per cent by the 1984 Census and 10.2 per cent by the 1994 Census.2 The 2007

Population and Housing Census counts almost 14 million Protestants, namely 18.6 per cent of the population, next to 43.5 per cent of Christians Orthodox and 33.9 per cent of Muslims." (page 150-151) ብለው ሲጽፉ አመንክና ትንጫጫ ጀመር፡፡ አባ ማትያስ "እርር ድብን በሉ!" ለማለት የምእመናን ቁጥር በአስደንጋጭ ሁኔታ እየቀነሰ መሆኑን በባለፈው "የሲኖዶስ" ስብሰባ ላይ እንደተናገሩ ሰምተሀል፡፡

መናፍቃኑና ወያኔ ይሔንን ስኬት ሊያገኙ የቻሉት ወያኔ ሥልጣን ከያዘ ጊዜ ጀምሮ በገዛ ሕገ መንግሥቱ ላይ "ለአምልኮ ከተፈቀደ ቦታ በስተቀረ ማንኛውም የሃይማኖት ተቋም በመንገድ፣ በመጓጓዣ መጠበቂያ (ፌርማታ)፣ በሥራ ቦታዎች፣ በመዝናኛ ቦታዎች ወዘተረፈ. ሃይማታዊ ትምህርት መስጠት ወይም መስበክ የተከለከለ ነው!" ብሎ የደነገገውን ድንጋጌ በመተላለፍ መናፍቃኑ በእነዚህ ቦታዎች ብቻም ሳይሆን ቤት ለቤት ሁሉ ሳይቀር እያንኳኩ ሰዉን ሰላም እየነሱ ያለ አንዳች ሥጋትና እቀባ የክህደት ስብከታቸውን በምእመናን ላይ እንዲረጩና እንዲያሰናክሉ በጎቻችንን ጠርገው እንዲወስዱ ከሕግ ውጪ በመፍቀዱ፣

በመላ ሀገሪቱ ባሉ የተለያዩ ቦታዎች የቀበሌ አዳራሾችንና "የእርሻ ሰብል" ይባል የነበረውን ድርጅት የእህል መጋዘኖችን ሌሎች የመንግሥት ንብረቶች የሆኑ አዳራሾችን ሁሉ ሕገ ወጥ በሆነና አግባብነት በሌለው አሠራር ለመናፍቃኑ መስበኪያ፣ መደንከሪያ፣ ማበጃ፣ ማጉሪያ፣ መዳሪያ እየሰጠ ለዚህ የጥፋት ተልእኳቸው የማያሰልስ ድጋፉና ትብብር በማድረጉ፣

አሁንም በሕገ መንግሥቱ የተከለከለውን ማለትም ማንኛውም የተራድኦ ወይም የግብረሰናይ ድርጅት ወይም የሃይማኖት ተቋም "ትምህርት ቤቶችን፣ ጤና ጣቢያዎችን፣ ወፍጮ ቤቶችን ወዘተረፈ. በመክፈት፤ እርዳታ በመለገስ ይንንም በመደለያነት በማቅረብ ሃይማኖትን መስበክና የቀደመ ሃይማኖታቸውን ለማስቀየሪያነት መጠቀም የተከለከለ ነው!" ቢልም ወያኔ ግን ይህ ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ በመናፍቃኑ ላይ እንዳይሠራና ዐይቶ ባለየ እንደፈለጉ እንዲፋንኑ በማድረግ ለመናፍቃኑ የማያሰልስ ድጋፉን እየሰጠና ምቹ ሁኔታዎችን እየፈጠረላቸው በዚህ ሕገ ወጥ ተግባር ተጠያቂ ሳያደርጋቸው በተለይ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶችን፣ ጤና ጣቢያዎችን፣ ወፍጮ ቤቶችን በማባበያነት እየከፈቱ ለተቸገሩ ዜጎች ወርኃዊ እርዳታ በመለገስ ሃይማትን እንዲክዱና ወደ እነሱ እንዲገቡ እያደረጉ እንዲስፋፉ በማድረጉ፣ በአንጻሩ ደግሞ ቤተክርስቲያንን ግን ከላይ እስከታች በሾማቸው ከሀዲያን አገልጋዮቹ አሳስሮ በማስቀመጥ፣ ይሄንን የጥፋት ዓላማውን አስቀድመው የነቁበትንና ሕዝቡን ለማንቃት ጥረት ሲያደርጉ የነበሩትን እንደ አለቃ አያሌውና እንደ ሐዋርያው አባ አምሃ ኢየሱስ ያሉ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያንን እያሳደደ በማጥፋት፣ ሌሎችንም ትክክለኛና የቤተክርስቲያን የመንጋው ጉዳይ የሚገዳቸውን አባቶችንን መምህራንን ካህናትን በየትኛውም ቤተክርስቲያን ላይ ማገልገል እንዳይችሉ በማድረግና በማባረር በማሳደድ በማጥፋት፣ እራሳቸው መናፍቃን ሰርገው እንዲገቡና የእኛን ቤተክርስቲያን መድረኮችና ንብረቶች ሁሉ እየተጠቀሙ እንዲስፋፉ በመደረጉ፣ (አባ ጳውሎስ ለመናፍቃኑ የተለያየ ዓይነት ድጋፍ ማድረጋቸው በመረጋገጡ ለመጨረሻ ጊዜ በተሳተፉበት "የሲኖዶስ" ስብሰባ ላይ "ሃይማትዎ ምንድን ነው?" ተብለው ተጠይቀው በማግስቱ ለሚቀጥለው ስብሰባ መልስ እንዲያቀርቡ ተቀጥሮ ጳጳሳቱ ቢጠብቁም አባ ጳውሎስ ግን ሳይገኙ መቅረታቸው ያታወሳል) እነዚህ እነዚህን በመሳሰሉ መሰናክሎችና ፈተናዎች ቤተክርስቲያን እንድትሽመደመድ በመደረጉና አሁንም እየተደረገ ስላለ ነው መንጋዋ ተጠርጎ የተወሰደው፡፡ ለዚህም ነው አቦይ ስብሐት ነጋ "የኦርቶዶክስን አከርካሪ ሰብረናል እንዳያንሰራራ አድርገን አዳክመነዋል!" ሲሉ የተናገሩት፡፡

መናፍቃኑ ቤተመንግሥትንና ቤተክህነትን ተቆጣጥረው መያዛቸው ለራሳቸው ይሄንን የመሰለ አስገራሚ ድል ሲያጎናጽፉ እኛን እንቅልፋሞቹን፣ ለአስመሳዮቹን፣ ሆዳሞቹን፣ ፈሪዎቹን ደግሞ እንዲህ ያለ በታሪክ ታይቶ ተሰምቶ የማያውቅ ውርደትና ኪሳራ ሊያከናንቡን ችለዋል፡፡

ይህንን ኪሳራ ያደረሱት "ከፓትርያርክ" ጽ/ቤት ጀምሮ እስከታችኛው የቤተክርስቲያን መዋቅር ያሉትን የበግ ለምድ ለብሰው የገቡ ተኩሎችና የወያኔ ካድሬዎችን ሳታውቃቸው ቀርተው ነው? በፍጹም! ይህ ሁሉ ሲሆን አንተን (ምእመናንን) ጨምሮ ከደብር አለቆች እስከ ጳጳሳት ወይም ሲኖዶስ የምትለው ድረስ ተኝቶ መንጋውን ከማስበላት ወይም ለሆዱ ሲል ኃላፊነቱን በመዘንጋት ዝም ብሎ ከማየትና ከማልጎምጎም በስተቀር እረኛ ነኝና ያስጠይቀኛል ብሎ ይሄንን የግፍ ድርጊት ተቃውመህ አይደለም ለመቃወም አስበህ ታውቃለህ? በፍጹም! እንዲያውም ጭራሽ እታሰራለሁ፣ ከሥራ እባረራለሁ እያልክ በመፍራት ሁልሽም የጥፋት ሥራቸው ተባባሪ ነው የሆንሽው፡፡

ይሄንን የወያኔንና የመናፍቃኑን ጥምረት ምን ፈጠረው? ቢባል ምንም የተሰወረ ነገር የለውም ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ እንደገለጽኩት ቤተክርስቲያን ክርስቶስ በቀየሰላትና ባዘዛት መንገድ የዘርና የቀለም ልዩነትን በሌለበት ሁሌታ ክርስቲያናዊ ሱታፌን (አንድነትን) መሠረት አድርጋ የምትሠራ የምትሰብክ መሆኗና የሕዝብ የሀገር አንድነትን የምትጠብቅ መሆኗ ይሄም ከወያኔ ጠባብ ብሔር ተኮር ፖለቲካዊ (እምነተ አሥተዳደራዊ) ርእዮተ ዓለም ጋር በቀጥና የሚጋጭ የሚቃረን የማይስማማ በመሆኑ ነው፡፡ የሚለው አንዱ ሲሆን ሌላው ደግሞ ወያኔ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንን የአማራ የህልውና መዋቅር አድርጎ ስለሚያያትና የነበረ ማንነቷን የረሳች፣ ከነበረ ማንነቷ ጋር የተለያየች ኢትዮጵያን ለመፍጠር የሀገሪቱ የቅርስ የታሪክ የማንነት የአጠቃላይ እሴቶች ግምጃ ቤት የሆነችው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መጥፋት መፍረስ አስፈላጊ ነው ብሎ ስለሚያምን ነው፡፡ ይሁንና እነኝህ ሁለቱ የወያኔ ምክንያቶች ሆነው ቢገኙም እንኳ "ወንጀል ነው" የሚል ሕግ በሀገሪቱ በሌለበት ሁኔታ ነው ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ የማጥፋት ተልእኮውን እየፈጸመ ያለው፡፡

እንዲህ ብሎ የሚያስበው የጥፋት ልጅ ወያኔ ከየትም ይምጣ ከየት ጠላት አድርጎ የሚያስባትን የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን ማጥፋት የሚፈልግ አጋር ማግኘትን እጅግ የሚፈልገው በመሆኑ እንኳንና በረሀ እያለ ጀምሮ ሁሉን አቀፍ እርዳታ እያደረጉለት ለዚህ ያበቁትና ስንት ውለታ እያለበት ባይኖርበትም እንኳ ከየትም ቢመጣ ለጥፋት ሥራው አጋዥ ኃይል ማግኘትን ትልቅ ዕድል አድርጎ ስለሚያስብ ይቀበላል፡፡ እናም እነኝህን ቀንዳሙንና ጅራታሙን የአጋንንት መንጋ በአንድ ያሰለፋቸው ምክንያት በቤተክርስቲያን ላይ የጋራ የጥፋ ዓላማ ያላቸው መሆናቸው ነው፡፡ ፍጹም ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ሔደው ለእነሱ ድል ለቤተክርስቲያን ኪሳራ ሊያስመዘግቡ የቻሉት፡፡

ይሄ ሁሉ ሲሆን ቤተክርስቲያንን የመጠበቅ ግዴታና ኃላፊነት አለበት የሚባለው "ሲኖዶስ" እና በጳጳስነቴ፣ በካህንነቴ፣ በመምህርነቴ፣ በሰባኪነቴ እረኛ ነኝ፣ አባት ነኝ፣ ምንትስ ነኝ የምትል አስመሳይ ሁሉ ይሄንን ሕገወጥና የውንብድና ተግባር ለማስቆምና ለመግታት ድርጊቱን በመቃወም ለራሳቸው ለሚመለከታቸው አንድ ያደረከው ነገር ኖሮ ያውቃል ወይ? እረኝነትህ የጠፋ በግ ማምጣት ቀርቶ መንጋውን በተኩላ ከማስበላት ታድጓል ወይ? ይሄንን የተኩላትና የወንበዴዎችን የውንብድና ተግባር ሳትቃወሙ በጎችንም ከመነጠቅ ሳትታደጉ እንዴት ነው እረኛ ነን ልትሉ የምትችሉት? ትንሽም እንኳ እግዚአብሔርን አታፍሩትም? በምንደኛነት በቅጥረኛነት ይህ ሁሉ ፈተናና ችግር እንደሌለ ሁሉ አፋቹህን መበመልካም ቃል እየቀባባቹህ ከርሳቹህን ለመሙላት ሌላ ሌላ ነገር ብትወሸክቱ እራሳቹህን እንጅ መድኃኔዓለም ክርስቶስን ማታለል የምትችሉ ይመስላቹሀል?

እነ አባ ማትያስ ማኅበረ ቅዱሳንን መዚጋት መበተን የሚፈልጉበት ምክንያት ሌላ ምንም ሳይሆን ማኅበሩ በሚሠራው ሥራ ሰርገው የገቡ መናፍቃንን አላሠራ በማለቱ፣ ተዳከመው እንዲጠፉ እየተደረጉ የነበሩትን የአብነት ትምህርት ቤቶችን በማጠናከሩ፣ ምእመናንን በማንቃቱ ወያኔና መናፍቃን "ቤተክርስቲያን ምእመናኖቿን በሙሉ ጨርሳ ተነጥቃ መዘጋት አለባት!" ብለው ከያዙትና ከሚያስቡት ጊዜ ስላዘገየባቸው ስለተቋቋማቸው ነው፡፡

ከላይ እንደዘረዘርኩት ይሄንን ያህል ቁጥር ያለውን መንጋ ከቤተክርስቲያን የነጠቁበት ያስኮበለሉበት መንገድ ወያኔ የገዛ ሕገ መንግሥቱን መናፍቃኑ ደግሞ እኛን ለማጃጃል "የዓለም አብያተክርስቲያናት ኅብረት" ብለው ያቋቋሙትን ማኅበር "የማኅበሩ አባላት ተከታይ ለማፍራት በሚንቀሳቀሱበት ወቅት ሙሉ ትኩረታቸውን በአሕዛብና በአረማዊያን ላይ ያደርጋሉ እንጅ አንደኛው የሌላኛውን የማኅበር አባል ተከታዮች ወይም አባላት አይወስድም!"

በማለት እንዳይወስድ የሚከለክለውን የጋራ ድንጋጌ ፍጹም በሻረ በተቃረነና በተጻረረ ውንብድና በተሞላበት መንገድ ስለሆነ እየወሰዱ ያከማቹት በስርቆት ወይም በውንብድና ወይም በሌላ ሕገወጥ መንገድ የተገኘ ንብረትና የተሠራ ሥራ ሕጋዊነትና ተቀባይነት ስለሌለው ለእነዚህ ወንበዴዎችና ሕገ ወጦች ሕገወጥና የውንብድና ሥራቸውን ያስፋፉ ዘንድ ምንም ዓይነት ሕጋዊ መስተንግዶ እንዲደረግላቸው የሚያዝ ሕግ በሀገራችን ስለሌለ 50 ሽህ የማጉሪያ አዳራሽ አይደለም አንዲት እንኳን ብትሆን ሊገነቡ የሚችሉበት ቦታ እንዲያገኙ እንዲሰጣቸው ፈጽሞ ፈጽሞ ልንፈቅድ አይገባም፡፡

እቃ አይደሉምና መልሱልን ማለት አንችልም እንጅ እንደ ሕጉ ቢሆን በጠቀስኩት ሕገ ወጥተግባር ውንብድናና ስርቆት የወሰዷቸውን በጎቻችን አንድ ሳናስቀር ባስመለስን ነበር፡፡ ነገር ግን በስርቆት በማጭበርበር በውንብድና የወሰዷቸው ተኩላና ወንበዴዎችን ግን ሌቦችና ሕገወጦች እንደመሆናቸው ከሀገራችን እንዲወጡልን መጠየቅና ማስወጣት ወደመጣበት መመለስ እንችላለን ይኖርብናልም፡፡ አለዛ ግን በተኩላ ተበልተህ ማለቅህ ነው፡፡

አስቀድሞ የቅኝ ግዛት ሰላይ በነበሩ አሁንም የራሳቸውን ስውር ዓላማ ለማስፈጸም ሃይማኖትን ሽፋን አድርገው በመንቀሳቀስ ሰርቀው አወናብደው አጭበርበረው በጥቅም አታለው የወሰዷቸው በጎች የነጣቂዎቻቸውን ማንነት በመላበስ የተኩላነት ሥራቸውን የሚሠሩ በመሆናቸው ካመሠራረታቸው ጀምሮ አሠራራቸው በሙሉ ሕገወጥና ውንብድና የተሞላበት በመሆኑ እነሱን ባገኘንበት ቦታ ሁሉ የመቃወም ተጋፍተው እየመጡ በጎቻችንን እንደመንጠቃቸው ሁሉንም ዓይነት ራስን የመከላከል እርምጃ በእነሱ ላይ የመውሰድ ሙሉ መብት እንዳለን ታውቆ ምእመናን ይሄንን በማድረግ መብታችንን፣ ደኅንነታችንን፣ ህልውናችንን፣ ማኅበራዊ ሰላማችንን እንድናስጠብቅ ጥሪየን ማስተላለፍ እወዳለሁ፡፡

መቸም ይሄንን ሁሉ የሚያደርጉት ለእኛ አስበው እኛን ለመጥቀም እነሱ እንደሚሉትም እኛ እግዚአብሔርን የማናውቅ ሆነን ከእግዚአብሔር ጋር ሊያስተዋውቁን የሚመስለው ዜጋ እንደማይኖር ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ በዚህች ሀገር መንፈሳዊ ጸጋ የቀናው አውሬው ዲያብሎስ ነው የላካቸው፡፡ ቅዱስ መጽሐፉ የሚመሰክረው ታሪክ የሚያረጋግጠው የእኛን በእግዚአብሔር አማኝነትና የእግዚአንሔር ልጅነት የእግዚአብሔር ሕዝብነት እንጅ እነሱ ከእግዚአብሔር መሆናቸውን አይደለም፡፡ ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል ትን. አሞ. 9፤7 መዝ 71/72፤9 መዝ. 73/74፤14 መዝ. 67/68፤31 "የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሯቹህን ዋኖቻቹህን አስቡ የኑሯቸውንም ፍሬ እየተመለከታቹህ በእምነት ምሰሏቸው ኢየሱስ

ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ዘለዓለምም ያው ነው ልዩ ልዩ ዓይነት በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ፡፡ ልባቹህ በጸጋ ቢጸና መልካም ነው እንጂ በመብል አይደለም በዚህ የሚሠሩባት አልተጠቀሙምና " ዕብ. 13፤7-9 እነሱ ግን እያመለኩትና እያገለገሉት ያሉት ሐሰተኛውን ክርስቶስ በዚህ ዘመን ኢየሱስ ነኝ ብሎ የሚመጣውን አውሬውን ኢየሱስ ለመሆኑ የተነሡበትን ዘመን የሚናገሩትንና የሚሠሩትን ማየቱ ብቻ በቂ ማስረጃ ነው፡፡ አውሬውን የሚከተሉ የሚያገለግሉ የዲያብሎስ ደቀመዛሙርት ናቸው፡፡

ለዚህም ነው እግዚአብሔር አብዝቶ የሚጸየፈውን ኃጢአትና በዚህ ኃጢአት ምክንያት ምድር እንድትጠፋ ተደርጋ የነበረችበትን (ዘፍ. 19፤5) ግብረ ሰዶምን ወይም ሰዶማዊነትን ተቀብለው ተከታዮቻቸውን ሥርዓት እየፈጸሙ ወንድን ከወንድ ሴትን ከሴት ጋር የሚያጋቡት እራሳቸው መሪዎቻቸውም ይሄንን ጸያፍ ኃጢአት ፈጻሚዎች የሆኑት፡፡

ይህ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው? የትኛው የእግዚአብሔር ቃል ነው ይሄንን የሚለው? የድንግል ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ይሄንን አስተምሯል? ወንጌል ማለት ይሄ ነው? ይህ ድርጊት በብሉይ ኪዳንም በአዲስ ኪዳንም ኃጢአት እንደሆነና ይሄንን የሚፈጽሙ ፍርድ እንደሚጠብቃቸው ከአጋንንት እንደሆኑ በግልጽ ተጽፎ እያለ ዘሌ.20፤13 ዘጸ. 23፤17 ሮሜ. 1፤22-27 1 ጢሞ. 1፤9-11 እነሱ ግን የአሳቹ አምላኪዎች ናቸውና በእነዚህ የእግዚአብሔር ቃሎች ተመክረው ተገስጸው ከዚህ ድርጊታቸው ሊታቀቡ ሊርቁ አልቻሉም፡፡

ጭራሽ እንዲያውም ይሄንን ጸያፍ እርኩሰት የሚያወግዙትን የእግዚአብሔር ቃሎች ሁሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሊያወጡት ሊሰርዙት እንደሆነ በይፋ ተናግረዋል፡፡ የመንግሥቶቻቸውንም ጡንቻ (የአውሬውን ራስና ቀንድ) በመጠቀም ግብረ ሰዶምን የማይቀበሉ ሀገራትን በማስገደድ እንዲቀበሉ ለማድረግ በከፍተኛ ጥረት ላይ ናቸው፡፡

"እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን እግዚአብሔር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው" ሮሜ 1፤28 "ስለዚህም ምክንያት በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በዓመፅ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ ፍርድን እንዲቀበሉ ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል" 2 ተሰ. 2፤11-12 የእግዚአብሔር ቃል ስለ እነዚህ ሐሰተኞች ሲናገረን "ነገር ግን ወንድሞች ሆይ እናንተ የተማራቹሀትን ትምህርት የሚቃወሙትን መለያየትንና መሰናከያን የሚያደርጉትን ሰዎች እንዳትመለከቱ እለምናቹሀለሁ፡፡ ከእነሱ ዘንድ ፈቀቅ በሉ እንደነዚህ ያሉት ለገዛ ሆዳቸው እንጂ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አይገዙምና በመልካምና በሚያቆላምጥ ንግግርም ተንኮል የሌለባቸውን ሰዎች ያታልላሉ" ሮሜ 16፤15-23 "እንደነዚህ ያሉ ሰዎች የክርስቶስን ሐዋርያት እንዲመስሉ ራሳቸውን እየለወጡ ውሸተኞች ሐዋርያትና ተንኮለኞች ሠራተኞች ናቸውና፡፡ ይህም ድንቅ አይደለም ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና እንግዲህ አገልጋዮቹ ደግሞ የጽድቅ አገልጋዮች እንዲመስሉ ራሳቸውን ቢለውጡ ታላቅ ነገር አይደለም፡፡ ፍጻሜያቸውም እንደ ሥራቸው ይሆናል፡፡ 2 ኛ ቆሮ. 11፤13 እያለ ስለአስመሳይነታቸው ቁልጭ አድርጎ በግልጽ ጽፎባቸዋል፡፡

የአውሬው መንፈስ እነሱን ተጠቅሞ የእግዚአብሔር ቃል በዘመኑ ፍጻሜ (በዚህ ዘመን) እንደሚመጡና ብዙዎችንም እንደሚያስቱ የተናገረላቸው ሐሰተኞች መምህራንና ሐሰተኞች ነቢያት በየ እልፍኙ (በየ አዳራሹ) ሐሰተኛውን ኢየሱስ እየሰበኩ እንደሚመጡ ብዙዎቹንም እንደሚያስቱ (ማቴ.24፤1-44) እንደተናገረው ሁሉ ይህችን ቅድስት ሀገር

ቅድስትነቷንም የእግዚአብሔር ቃል ያረጋገጠላትን ሀገርና ሕዝብ ቅድስናዋን ለማስጣል ሕዝቧን ለማርከስ ለማስካድ በአጋንንት መንፈስ ተሞልተው ታጥቀው ተነሥተዋል፡፡

ሁሉም ሊሰማው የሚፈልገውን ነገር እየተናገሩ ክርስቶስ የመጣው የሰው ልጆችን በኃጢአት ለመዋጀት ይመስል፣ ለኃጢአት አርነት ሊያወጣ የመጣ ይመስል ከቅዱስ ቃሉና ከክርስቶስ ኢየሱስ ዓላማ በተጻራሪ ቃሉን ቆንጽለው በማውጣት "በጸጋው ድነሀል! ምንም ብትሠራ አትጠየቅም ስላመንክ ድነሀል!" እያሉ ሰው በሠራው ኃጢአት እንደማይጠየቅና መሥራት የፈለገውንም ሁሉ ኃጢአት ነው እርኩሰት ነው ሳይል በነጻነት እንዲሠራ ይሄንን ሁሉ አድርገም እንደማይኮነን እየሰበኩ በማወናበድ እየወሰዱት ይገኛሉ፡፡

ይህ የአውሬው የሐሳዊ መሲሑ ኢየሱስ የዲያብሎስ ትምህርት እንጅ የድንግል ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል አይደለም፡፡ "ማመን እማ አጋንንትም ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል" ያዕ.2፤17-26 ነው የሚለው ቃሉ፡፡ የድንግል ልጅ ኢየሱስ ወንጌል የሚለው "ብትወዱኝስ ትዕዛዜን ጠብቁ" ዮሐ. 14፤15 "ትዕዛዛቱንም ብንጠብቅ በዚህ እንዳወቅነው እናውቃለን አውቄዋለሁ የሚል ትእዛዛቱንም የማይጠብቅ ውሸተኛ ነው እውነትም በእርሱ ውስጥ የለም፡፡ ቃሉን ግን የሚጠብቅ ሁሉ በእርሱ የእግዚአብሔር ፍቅር በእውነት ተፈጽሟል" 1ኛ ዮሐ. 3፤5 እንግዲህ በኢየሱስ የሚያምን ማለት ብዙዎች እንደሚያስቡት በቃ አምኛለሁ ማለት ሳይሆን ሮሜ. 8፤1-8 እንደተገለጸው የሥጋን ነገር ጣል እርግፍ አድርጎ የመንፈስን ነገር መያዝ ማለት እንደሆነ በማያሻማ መልኩ ግልጽ አድርጎታል፡፡ አሁንም ቢሆን ግን የእግዚአብሔር ቸርነት ካልታከለበት በስተቀር በሥራው ብቻ የሚጸድቅ የለም! ምክንያቱም ምንም ያህል የጽድቅ ሥራ ቢኖረን ነቢዩ ኢሳይያስ እንደተናገረው "ጽድቃችንም ሁሉ እንደመርገም ጨርቅ ነውና" ትን. ኢሳ. 64፤6 ሐዋርያትም "ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን እውነትም በእኛ ውስጥ የለም" 1ኛ ዮሐ. 1፤9 ይላሉና ከሠራነው የጽድቅ ሥራ ጋር ቸርነቱ ታክሎበት የምንጸድቅ በመሆኑ "እንዲሁ በጸጋው (በቸርነቱ)" ጸደቅን ማለት ይቻላል እንጅ እርኩሰት እየተፈጸመ ንስሐን ሳያውቁ "በጸጋው ጸድቀናል" የሚባል ነገር የአጋንንት ወንጌል ካልሆነ በስተቀር የክርስቶስ ወንጌል ይሄንን ፈጽሞ አላለም፡፡ እናም ቃሉ የማያሻማ በመሆኑ ማምታታት ማወናበድ አይቻልም፡፡

"እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ፡፡ ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታል፤ ስለ እኔ ግን ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ያገኛታል፡፡ ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል? ወይስ ሰው ስለ ነፍሱ ቤዛ ምን ይሰጣል? የሰው ልጅ ከመላእክቱ ጋር በአባቱ ክብር ይመጣ ዘንድ አለውና ያን ጊዜም ለሁሉ እንደ ሥራው ያስረክበዋል፡፡" ማቴ. 16፤24-28 ጌታ ያለውን ልብ አላቹህ? "ለሁሉ እንደሥራው" ነው ያለው፡፡

ይህ ሁሉ ግልጽ የጌታ ቃል በብዛት ተጽፎ እያለ መናፍቃኑ ግን ያለማወቃቸው አለማወቅ አይሁድ በክርስቶስ ሳያምኑ ሕግን በመፈጸም ብቻ እንደሚጸድቁ ያስቡ ነበርና ሐዋርያት ለአይሁድ በክርስቶስ ሳያምኑ ሕግን በመፈጸም ብቻ መዳን እንደማይችሉ የተናገሩትን ቃል ሮሜ. 3፤11-20 እንዲሁም ገላ. 2፤16 በመጥቀስ በክርስቶስ አምነን "ትዕዛዜን ጠብቁ" ያለንን የአምላካችንን ቃል አክብረን ሕጉን ትዕዛዙን ለመጠበቅ ለምንጥረው ለእኛ እየጠቀሱ "ሕግን መጠበቅ አያድንም

ማመን ብቻ ነው የሚያድነው" እያሉ ሲጠቅሱ ይደመጣሉ። ሲጀመር ቤተክርስቲያን ሕግን መጠበቅ ብቻ ያድናል ብላ አታውቅም። ቃሉ ግን "በእግዚአብሔር ፊት ሕግን የሚያደርጉ ይጸድቃሉ እንጅ ሕግን የሚሰሙ ጻድቃን አይደሉምና" ሮሜ. 2፤13 ሐዋርያትም ከጌታ እንደመረዳታቸው ሁሉ ሲሰብኩ ምን አሉ "ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል" አሉ የሐዋ. ሥራ 14፤22 "በኋላየ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንም ዕለት ዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ" ሉቃ. 9፤23 ቃሉ መስቀሌን ሳይሆን መስቀሉን በማለት የየራሳችንን መስቀል ነውና የሚለው መስቀል መሸከም ማለት ክርስቶስ ስለ እኛ የተቀበለውን መከራ በማሰብ እንደተራብ እንደተጠማ እንደወደቀ እንደተነሣ ሁሉ አብዝቶ በመጾም መራብ፣ አብዝቶ በመጸለይ በመስገድና እራስን በማድከም እንደየ አቅማችን ክርስቶስን በመከራው መምሰል ማለት ነው።

ቅዱሳን ግን ከዚህም አልፈው ማለትም አብዝቶ ከመጾም ከመጸለይ ከመስገድ ባሻገር በየገድላቸው ተጽፎ እንደምናገኘው ሁሉ ክርስቶስ የተቀበለውን መከራ ያህልም እንኳን ባይሆን ምክንያቱም የእሱን መከራ ማንም የሚችል የለምና። ነገር ግን እንዳስቻላቸው መጠን ብዙ ዓይነት ለእኛ ለሥጋውያኑ ፈጽሞ ሊታሰብ የሚከብዱ የመከራ ዓይነቶችን በየገዳሙ፣ በየበረሀው፣ በየዋሻው፣ በየፍርኩታው ስለ ፍቅሩ ስለስሙ ክብር ስለአምላክነቱ ይቀበላሉ በመከራውም ይመስሉታል።

አስቀድሞም ቃሉ ስለ እነሱ "የክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑት ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉት" ገላ. 5፤24 እንዳለው ሁሉ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ሥጋቸውን ብዙ መከራ እንዲቀበል በማድረጋቸው፣ ወንጌልን ቃል በቃል በሕይዎታቸው ተርጉመው በማሳየት እንደዛ የሆኑለት አምላካቸው መድኃኔዓለም ክርስቶስም ለብዙ ክብርና ጸጋ አብቅቷቸዋል። የቅዱሳን ሕይዎት ወይም ገድል ማለት የሚነበብ የሚታይ የሚደመጥ ወንጌል ማለት ነው። ቅዱሳን ቸርነቱ ታክሎበት እንደ ክርስቶስ ቃል እንደ ወንጌል መኖር እንደሚቻልና ወንጌል ማለት ውሸት ሊፈጸም የማይችል ተረት ሳይሆን እውነትና ሊፈጸም የሚችል የአምላክ ቃል መሆኑን አሳይተው በሕይዎታቸው ተርጉመው ያረጋገጡ የእምነት አርበኞች የሚነበቡ ወንጌል ናቸው።

የአውሬው ደቀመዛሙርት ግን ኢየሱስ በቃሉ"እውነት እውነት እላችኋለሁ! በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፤ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል!" ዮሐ. 14፤12 ብሏልና ቅዱሳን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የሠሩትን ተአምራት ሁሉ "በአስማት ነው!" በማለት የክርስቶስ ቃል ሊፈጸም የማይችልና ሐሰት አድርገውታል። እንግዲህ እምነታቸው ይሄንን ያህል ነው። እንደቃሉ ቢኖሩ በመከራው ቢመስሉት ግን ቅዱሳኑ የተጎናጸፉትን ኃይል በተጎናጸፉት ነበር። አይችሉማ! እነሱ የሚፈልጉት እራሳቸውን በምቾት በድሎት መጠበቅ ነው።

በምቾት በድሎት ሆኖ ደግሞ የክርስቶስ ኃይልና ጸጋ አይገኝም! እንዲህ ዓይነት ክርስትናም የለም! "የተጠራቹህት ለዚህ ነውና ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉት ምሳሌ ትቶላቹህ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሏልና" 1 ጴጥ. 2፤21 "ቀንበሬን በላያቹህ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና ለነፍሳቹህም ዕረፍት ታገኛላቹህ" ማቴ. 11፤29

ከዚህ በላይ እንደምን አድርጎ በግልጽ ይናገር? ክርስትና ማለት መከራ መቀበል እንጅ "አንድ ጊዜ በጸጋው ድነናል!" በማለት የሥጋ ድሎትን ምቾትን ዓለምን ማሳደድ ማለት አይደለም፡፡

ሌላም እንጨምር? "ክርስቶስም በሥጋ ስለ እኛ መከራን ስለተቀበለ ከእንግዲህ ወዲህ በሥጋ ልትኖሩ በቀረላቹህ ዘመን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንጅ እንደ ሰው ምኞት እንዳትኖሩ እናንተ ደግሞ ያን ሐሳብ እንደ ዕቃ ጦር አድርጋቹህ ያዙት በሥጋ መከራን የተቀበለ ኃጢአትን ትቷልና" 1 ጴጥ 4፤1 "ሞትን በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ በእርሱ ጋር እንተባበራለን" ሮሜ 6፤5 ይሄ ሲባል ግን ሁሉም ሕዝበ ክርስቲያን መናኝ የበረሀ ባሕታዊ መሆን አለበት ሀገርም ወና ትሁን ትውልድም ይቋረጥ ማለት አይደለም፡፡

ክርስቶስም ለዚህ ጥያቄ መልስ ሰጥቷል "ለተሰጣቸው ነው እንጅ ለሁሉ አይደለም" ማቴ. 19፤11 ብሎ "ሊቀበለው የሚችል ይቀበለው አላቸው" ማቴ. 19፤12 የተቀረነው ደግሞ በዓለም ሆነን ሃይማኖታችንን ጠብቀን ሥራችንን እየሠራን ሀገር እያለማን ቤተክርስቲያን በዓለም ለሚኖሩ ክርስቲያኖች እንደየአቅማቸው የደነገገችውን የጾም የጸሎት የሥግደት የሌሎችንም ትሩፋቶች ሥርዓት እየፈጸምን ክርስትናን እንኖራለን ማለት ነው፡፡ እንጂ የሌለ ነገር እየተጠቀሰ ክርስቶስ እንዲህ ሆኖልኛል ምንትስ እየተባለ መረን ተለቀ የሚኖር ክርስትና ጨርሶ የለም፡፡

ዚህም ነው ቃሉ "ወንድሞች ሆይ እምነት አለኝ የሚል ሥራ ግን የሌለው ሰው ቢኖር ምን ይጠቅመዋል? እምነቱስ ሊያድነው ይችላልን?....ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደሆነ እንደዚሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው" ያዕ. 2፤14-26 "በጠበበው ደጅ ግቡ ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጁ ሰፊ መንገዱም ትልቅ ነውና ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው ወደ ሕይዎት የሚወስደው ደጁ የጠበበ መንገዱም የቀጠነ ነውና የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው፡፡

የበግ ለምድ ለብሰው (ክፉ ሆነው ሳለ ለማታለል በማስመሰል በበግ የሚመሰሉትን የጻድቃንን ጠባይና ሥራ እየሠሩ) ከሚመጡባቹህ በውስጠቸው ግን ነጣቂዎች ተኩላዎች ከሆኑ ሐሰተኞች ነቢያትና ሐሰተኞች መምህራን ተጠንቀቁ.... በሰማያት ያለው የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጅ ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም፡፡ በዚያን ጊዜ ብዙዎች ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን? በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል፡፡ የዚያን ጊዜም ከቶ አላውቃቹህም እናንተ ዓመፀኞች ከእኔ ራቁ ብየ እመሰክርባቸዋለሁ" ማቴ. 7፤13-23 በስምህ ይሉኛል አለ እንጅ በስሜ አለማለቱን ልብ ይሏል፡፡

ሐሰተኞች ክርስቶሶች እንደሚመጡና በእነሱም ስም የተጠቀሰው ሁሉ ተአምራትና ከዚያም በላይ እንደሚያደርጉ አስቀድሞ ተናግሯልና፡፡ ማቴ.24፤25 " አመንዝሮች ሆይ ዓለምን መውደድ ለእግዚአብሔር ጥል እንደሆነ አታውቁምን? እንግዲህ ለዓለም ወዳድ ሊሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኗል፡፡.....እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል፡፡ እናንተ ኃጢአተኞች እጆቻቹህን አንጹ ሁለት ሐሳብም ያላቹህ እናንተ ልባቹህን አጥሩ፡፡

ተጨነቁና እዘኑ አልቅሱም ሳቃቹህ ወደ ኃዘን ደስታቹህም ወደ ትካዜ ይለወጥ፡፡ በጌታ ፊት ራሳቹህን አዋርዱ ከፍ ከፍም ያደርጋቹሀል" ያዕ. 4፤4-10 እንግዲህ ቃሉ እንዳረጋገጠልን የሃይማኖተኝነት ወይም የመንፈሳዊነት መንገድ ይሄው ነው ሌላ የለም፡፡ የጌታ ቃል የሚለው ይሄንን ከሆነ እነሱ ከየት አምጥተው እንደሚዘባርቁ ልብ ያለው ልብ ይላል፡፡

እናም የሰዎቹ ማንነት ይሄ ከሆነ ዘንዳ ዓላማቸው ሌላ እንጅ ሃይማኖት አይደለም ማለት ነው፡፡ እውነት የእምነት ሰዎች ቢሆን ኖሮ ሲጀምር አስተምህሯቸው ከላይ እንደገለጽኩት ሁሉ ይሄንን ያህል ከወንጌል የራቀ የተጻረረ ባልሆነ ነበር፣ እዛው ሀገራቸው ላይ የጠፋው መላ ሕዝባቸው ላይ ባተኮሩ ነበር፣ የገዛ ሕዝባቸው ሃይማኖትን እንደ ኋላ ቀር አስተሳሰብ አድርጎት በዘመናዊነት በዓለማዊነት በእርኩሰት ፍቅር አብዶና ተነድፎ በእግዚአብሔር አለማመንን ሃይማኖቱ አድርጎ የጠፋውን ሕዝባቸውን ሰይጣኒዝም ብለው ሰይጣንን በግላጭ የሚያመልክ ሕዝባቸውን አስተምረው ለመመለስ ጥረት አድርገው ተገልጋይ ከማጣታቸው የተነሣ ለነዳጅ ማደያ አገልግሎቶችና ለገበያ አዳራሽ አገልግሎት ተሸጦ እያለቀ ያለውን የማምለኪያ ስፍራዎቻቸውን በአማኞቻቸው በሞሉ ነበር፡፡

ነገር ግን ዓለማቸው ይሄ አይደለምና ሳይፈሩና ሳያፍሩ የእግዚአብሔር ቃል ምስክር ያለውን ሕዝብ በኃይማት ሽፋን መጥተው በክህደት አዘቅት ውስጥ በማስመጥ ዲያብሎስ የሰጣቸውን ተልእኮ ለመፈጸም ይሄው ይሯሯጣሉ፡፡

እኛ መቸ እምነት ቸገረን? ካዘኑልን ከድህነት ወጥተን እራሳችንን እንድንችል ሊያደርገን የሚችል ስንት ሊያደርጉልን የሚችሉት ነገር ነበረ አይደል፡፡ ምን አለ አሁን ይሄንን 50,000 የማምለኪያ አዳራሽ እንሠራበታለን ያሉትን በቢሊዮኖች (በብልዮች) ዶላር የሚቆጠረውን ገንዘብ መሠረተ ልማት እንድንገነባበት፣ ሆስፒታል፣ ትምህርት ቤት የመሳሰሉትን እንድንገነባበት ቢሰጡን ምን ነበረበት**?** አሃ! እንዲህማ ካደረጉ እኛ ልንጠቀም ነዋ! ዓላማው መች ይሄ ነው፡፡ ዓለማው አጋንንታዊና በዚህች ሀገር ዘርፈ ብዙ ጥፋት ማምጣት፣ በማኅበራዊ ቀውስ ተዘፍቃ እንድትቀር ማድረግ ነው፡፡

ይህ እንዲሆን ፈጽሞ መፍቀድ አይኖርብንም፡፡ የእስካሁኑ ዝምታህ ምን እንዳስከፈለህ ዓይተሀል፡፡ የወሬ ዘመን አብቅቷል፡፡ ከዚህ በኋላ ጨርሰህ መጥፋት ካልፈለክና የሚጠበቅብህን ክርስቲያናዊ ኃላፊነት ባለመውሰድህ በእግዚአብሔር ፊት ተጠያቂ መሆን ካልፈለክ ልትወስደው የሚገባህ እርምጃ ይሄና ይሄ ብቻ ነው፡፡ "ወዳጆች ሆይ! ስለምንካፈለው ስለ መዳናችን ልጽፍላችሁ እጅግ ተግቼ ሳለሁ ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለ ተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ እየመከርኋችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ" ይሁ. 1፤3 ይሄንን ማድረግ ካልቻልን ግን በእግዚአብሔር ፊት ከእነሱ በከፋ ተጠያቂ እንደምንሆን ሊታወቅ ይገባል፡፡

ይሄንን ማድረግ አልችልም የምትለው የእራስህን ደኅንነት ለመጠበቅ፣ ሕይወትህን ለማደላደል ለማመቻቸት፣ ችግር ላይ ላለመውደቅ፣ ጣጣ ውስጥ ላለመግባት ነው አይደል እንዴ አንድ ጊዜ "ፖለቲካ ነው" አንዴ ምንትስ ነው እያልክ ክርስቲያናዊ ግዴታህንና ኃላፊነትህን ላለመወጣት ቤተክርስቲያንን እንዲህ አጋድመው ሲያርዷት በዝምታ የተመለከትከው? ጥሩ! ደኅንነትህ የሚጠበቀው፣ በልተህ ማደር የምትችለው ባንተ ብልጠት እንጅ በእግዚአብሔር ጥበቃና መጋቢነት እንዳልሆነ አስበህ አምነህ በክርስቲያንነትህ ክርስቶስ ኢየሱስ የጣሉብህን አደራ ከመወጣት ሸሽተሀል ወደ ኋላ ብለሀልና ለዚህ

ከህደትህ እሱ ደግሞ እንዴት አድርጎ በምን አቀጣጥ እንደሚቀጣህ፣ በምን አመታት እንደሚመታህ ታያለህ ጠብቀው! ያኔ ደኅንነትህን፣ ሰላምህን፣ የተመቻቸ ኑሮህን ታገኛታለህ፡፡

በእርግጥም የደኅንነትህ፣ የሰላምህ፣ የኑሮህ ዋስትናና ጠባቂው አንተው እራስህ እንጅ እግዚአብሔር እንዳልሆነ ታረጋግጣለህ እሽ? ከእግዚአብሔር ያልተሰጠህን ያልተፈቀደልህን ደኅንነት ሰላምና ምቾት ባንተ ብልጠት ታገኛታለህ ይመስልሀል? አሁን አንተ ታዲያ ምንህ ነው ክርስቲያን? ልዑል እግዚአብሔር የሚጠበቅብንን ክርስቲያናዊ ኃላፊነት እንድንወጣ አስችሎን ቅድስት በቤተክርስቲያንን ከጥፋት ይታደግልን ዘንድ ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን አሜን!!!

ስለዚህ የቤተክርስቲያን ፈተና ዝርዝር ጉዳዮችን መረዳት ከፈለጉ በዚህ ጉዳይ ከጻፍኳቸው ከፊሎቹ ርእሳቸው የሚከተለው ነው ጎግል አድርገው ሊያገኟቸው ይችላሉ፡- ደኅና ሁኚ ቤተክርስቲያን፣ ፖለቲካና ሃይማኖተኝነት የሚያቃርናቸው ነገር አለን?፣ የኢትዮጵያ (የክርስቶስ) ቤተክርስቲያን የጣር ድምፅ!፣ የተባረኩ ሀገራት ወይስ የተረገሙ? የተባረኩ ሕዝቦች ወይስ የተረገሙ?፣ የቅዱስ ሲኖዶስን ስምና ሥልጣን የተጠቀመው የመናፍቃኑ መግለጫ!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

amsalugkidan@gmail.com